# ኅብረት ለምርጫ

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ


# የኢትዮጵያ ሚዲያ ተደራሽነት ሕጎች እና በምርጫ ወቅት የሚዲያ ተደራሽነት ለምርጫ ባለድርሻ አካላት ላይ የተዘጋጀ

## የኅብረት ለምርጫ ፖሊሲ ፍሬ ሃሳብ


ግንቦት 2015 ዓ.ም

# ማውጫ


| | |
|---|---|
| ዋና ማጠቃለያ | 4 |
| ዋና ዋና ነጥቦች | 6 |
| መግቢያ | 7 |
| ስለ ኢትዮጵያ ምርጫ የሚዲያ ሽፋን የህግ ማዕቀፎች | 7 |
| የኀብረት ለምርጫ የሚዲያ ክትትል ክፍል | 8 |
| በ6ኛው ጠቅላላ ምርጫ ወቅት የነበረ የሚዲያ ተደራሽነት ለምርጫ ባለድርሻ አካላት | 8 |
| መደምደሚያ/ምክረ ሃሳቦች | 10 |

# ዋና ማጠቃለያ






Photo: NEBE




ይህ የፖሊሲ ማብራሪያ በመገናኛ ብዙሃን እና በምርጫ መካከል ያለውን ግንኙነት አስፈላጊነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በኢትዮጵያ 6ተኛው ጠቅላላ ምርጫ ዙሪያ ያሉትን ተግዳሮቶች፣ አንድምታዎች እና ተስፋዎች እና የመገናኛ ብዙሃን የተለያዩ የምርጫ ባለድርሻ አካላትን ተደራሽነት ይዳስሳል። ከዚህ ባለፈም የሚዲያ ተቋማት የጋዜጠኝነት ሞያ ስነ-ምግባር አክብረው በምርጫው ሂደት ላይ ሚዛናዊ ሽፋን መስጠት እንዳለባቸው ያትታል። በተጨማሪም የመራጮች ትምህርት የሚዲያ ሽፋን ማሳደግ እና ሴቶችን ጨምሮ ሁሉም ባለድርሻ አካላት በምርጫ ወቅት በሚዲያ ሽፋን በበቂ ሁኔታ እንዲወከሉ የማድረግን አስፈላጊነት አጉልቶ ያሳያል።

በኅብረት ለምርጫ የሚዲያ ክትትል ክፍል ዘገባ ላይ በመመስረት፤ 6ተኛው ጠቅላላ ምርጫ በተካሄደበት ወቅት፣ ከምርጫ ጋር የተያያዙ ርዕሰ ጉዳዮች ብዙውን ጊዜ በመገናኛ ብዙኃን ሽፋን ቢያገኙም፤ ነገር ግን የሚዲያ ሽፋን በሌሎች ከምርጫ ጋር ያልተገናኙ የፖለቲካ ጉዳዮች () አብላጫ የሆኖ ሽፋን አግኝተው ነበረ። በምርጫ ክርክሮች ላይ 12 የፖለቲካ ፓርቲዎች ቢሳተፉም በትላልቅ የክርክር መድረኮች 5 የፖለቲካ ፓርቲዎች ብቻ ነበር የተሳተፉት። የጋዜጠኝነት ሞያዊ ሥነ ምግባርን አክብሮ መዘገብ ላይ ከሚዲያ ሚዲያ ልዩነት ነበረ። ከዚህም ባለፈ አብዛኛው ሚዲያ የምርጫ ቅስቀሳን ሚዛናዊነት በጠበቀ መልኩ ከመገናኛ ብዙሀን ህጎች እና ከምርጫ ቦርድ መመሪያዎች ጋር በተስማማ ሁኔታ ማቅረብ አልቻሉም ነበር። ገዥው ብልፅግና ፓርቲ ከሌሎች የምርጫ ባለድርሻ አካላት ጋር ሲነጻጸር ከፍተኛውን ሽፋን ያገኘ ሲሆን በተጨማሪም ሚዲያዎች ከምርጫ ጋር በተገናኘ ለሴቶች የሰጡት ሽፋን በጣም አነስተኛ ነበር፡፡

በኢትዮጵያ የሚዲያ ዘርፍ በምርጫ ወቅት ተገቢውን ሚና እንዲጫወት ለማድረግ ከቀደምት የስኬት ተሞክሮዎች ትምህርት በመውሰድ እና በመጪው ምርጫ የሚዲያው ዘርፍ የላቀ ሚና እንዲኖረው መሻሻል በሚገባቸው ዘርፎች ላይ አተኩሮ ሊሰራ ይገባል። ይህ ካልሆነ ግን ሚናው ተቆርጦ በቀደመው ምርጫ ወቅት እንደነበረው ይቆያል።

# ዋና ዋና ነጥቦች

- በ6ተኛው ጠቅላላምርጫ ወቅት የመራጮች ትምህርት ዝቅትኛ ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ሲሆን በዚህም የተነሳ ብዙ ተመልካች ሊያይ/ሊያዳምጥ በሚችልበትት ጊዜ የተላለፉ የመራጮች ትምህርት ይዘቶች ውስን ነበሩ።
- የመራጮች ትምህርትን ለማድረስ ጥቅም ላይ ከዋሉት መንገዶች አንዱ የምርጫ ክርክር የነበረ ሲሆን ፣ በክርክሮቹም 12 የሚሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተሳትፈዋል። ምንም እንኳን ከተደረጉት ክርክሮች መካከል በአራቱ ላይ ባይሳተፍም በክርክሮቹ ጎልቶ የወጣው ገዢው የብልጽግና ፓርቲ ነበር። ይህ ለፖለቲካ ፓርቲዎች በእኩልነት መርህ ላይ ያልተመሰረት ሽፋን የዴሞክራሲ ሂደቱን ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከማሳደሩ እንዲሁም ሚዲያዎች ለሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች እኩል ተደራሽነትን እንዲያረጋግጡ ከሚጠይቀው የሕግ መርህ ጋር የሚጣረስ ነው።
- በጥቅሉ በሚዲያ ለፖለቲከኞች የተሰጠው ሽፋን መድሏዊ ያልነበረ እና የፖለቲካ ቡድኖችን በአዎንታዊ መልኩ ሽፋን የሰጠ ነበር። ሆኖም በተወሰነ መልኩ ሚዲያዎች በተለይም በአዲስ አበባ መገናኛ ብዙሃን፣ በአማራ ቲቪ እና ዋልታ ቲቪ የተላለፉ ዘገባዎች ለፖለቲካ ግለሰቦች ወይም ቡድኖጽ ገለልተኛ ያሆነ አለፍ ሲልም አሉታዊ ሽፋኖችን ሰጥተዋቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ እነዚህ ሚዲያዎች አብዛኛውን የአየር ሰአታቸውን ለገዢው ፓርቲ ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ ዘገባ በመስራት ላይ አውለዋል። ይህ በስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ የነበረን ግልጽ የሆነ የፖለቲካ እና የምርጫ ወቅት ዘገባ እንደነበር ያሳያል።
- ዘርፉ ለሴቶች የሰጠው ሽፋን በጣም አነስተኛ ነበር። የሚዲያ ክትትል ክፍል ሪፖርት እንደሚያሳየው በምርጫ ክርክር ከተሳተፉ ተከራካሪዎች መካከል የሴቶች ቁጥር ከ20 በመቶ ያነሰ ነበር። የሴቶችን እና የአካል ጉዳተኞች በፖለቲካ ሂደት ውስጥ በአነስተኛ መልኩ የሚዲያ ሽፋን ማግኘታቸው የተገለሉ እና ልዩ ትኩረት የሚያሻቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በፖለቲካያላቸውን መብት እና ተሳትፎ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል።



# መግቢያ

የሚዲያ ተደራሽነት ዜጎች መረጃን ከብሮድካስት፣ ከዲጂታል፣ ድረ-ገጽ ፣ ጋዜጣ እና ሌሎች መሰል የመረጃ ምንጮችን ተጠቅመው መረጃ የማግኘት መብታቸውን ያመለክታል።[1] በዴሞክራሲያዊ ስርአት ውስጥ የመገናኛ ብዙሃን የምርጫ ሂደት በተሳለጠ መልኩ እንዲካሄድ ትልቅ ድርሻ ያበረክታሉ። በምርጫ ወቅት መገናኛ ብዙሃን ከተለያዩ የምርጫ ባለድርሻ አካላት ጋር የተገናኙ መረጃዎችን ለማድረስ እንደ መሳሪያ ያገለግላሉ። ነገርግን የኢትዮጵያ የሚዲያ ዘርፉ ትኩረቱን በዋናነት መንግስት-ተኮር የሆኑ የምርጫ ዘገባዎች በመስራት ላይ ብቻ ያተኩራል በሚል የሰላ ትችት ይሰነዘርበታል።[2]

ጥናቶች እንደሚያሳዩት በ1997 ዓ.ም በተደረገው ምርጫ ወቅት የህትመት ሚዲያው ለምርጫው ከፍተኛ ሽፋን ሰጥቶ ነበር። ነገርግን ከምርጫው ማግስት አንስቶ መንግስት በርካታ የህትመት ሚዲያዎችን መዝጋቱ ፤ ጋዜጠኞችንም ማሰሩ የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው ። ይህ በሚዲያ ላይ የተወሰደ የማዳከም እርምጃ የሚዲያ ነጻነትን አሉታዊ በሆነ መልኩ የጎዳ ሲሆን ይህንንም ተከትሎ ከ2001 ዓ.ም. እስከ 2011 ዓ.ም. ባሉት አመታትውስጥ 260 ጋዜጦች እና መጽሄቶች በመንግስት ተዘግተዋል።

አንድ ምርጫ ዴሞክራሲያዊ እና የህብረተሰቡን እውነተኛ ፍላጎት የሚያንጸባርቅ እንዲሆን ሁሉም የመገናኛ ብዙሃን ለሁሉም የምርጫ ባለድርሻ አካላት እኩል ተደራሽ መሆን አለባቸው። ካለነፃ የመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ ጠንካራ የዴሞክራሲ ስርአትን መገንባት አዳጋች ነው። በመሆኑም በተለያዩ የምርጫ ደረጃዎች ላይ ሚዲያዎች የሚሰሯቸውን ዘገባዎች እና የሚሰጧቸውን ሽፋኖች መከታተል እንዲሁም መተንተን ወሳኝነት ያለው ተግባር ነው። በምርጫ ወቅት የሚዲያ ከትትል ተግባር መከናወኑ የምርጫ የሚዲያ ዘገባ ከተፅዕኖ ነፃ፣ ገለልተኛ ፣ ሙያዊ ሃላፊነት በተሞላበት መልኩ እንደተከናወነ ለመረዳት ያስችላል።

# ስለ ኢትዮጵያ ምርጫ የሚዲያ ሽፋን የህግ ማዕቀፎች

በኢትዮጵያ በፌዴራል ሕገ መንግሥት፣ የሚዲያ ተኮር እና የምርጫ ልዩ ሕጎችና ደንቦች ውስጥ የመገናኛ ብዙኃንን ተደራሽነት የሚቆጣጠሩ በርካታ ሕጋዊ ሰነዶች አሉ። በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 29 የአመለካከት እና የሀሳብ ነፃነትን ይደነግጋል። ከሌሎች አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ ህገ መንግስቱ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ላይ መሰረታዊ መብቶች እና ገደቦችን ዘርዝሯል። ይህ የህግ ማእቀፍ ሚዲያው የግለሰቦችን እና የሀገርን ደኅንነት ባገናዘበ መልኩ ሊንቀሳቀስ እንደሚገባም ያትታል። በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 29(6) ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው የወጣቶችን ደህንነት፣ የግለሰቦችን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ በሚዲያ ላይ የሕግ ገደቦች ሊጣሉ ይችላሉ። ማንኛውም የጦርነት ፕሮፓጋንዳ እንዲሁም የሰውን ክብር ለመጉዳት የታሰበ አስተያየት ወይም አመለካከት ማሰራጨት በህግ የተከለከለ ነው።

ከህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች በተጨማሪ ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ እና የሚዲያ ነፃነትን የሚያበረታቱ እና የሚጠብብቁ የተለያዩ ህጎች ወጥተዋል። በየካቲት 2013 ኢ.ም የኢትዮጵያ የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት ነጻ የሚዲያ ምኅዳር ለመመስረት እንደ አንድ እርምጃ ተደርጎ የሚነገርለትን አዋጅ አጽድቋል። ይህ አዋጅ በምርጫ ወቅት የሚዲያ እንቅስቃሴዎችን የሚቆጣጠሩ የተለያዩ ደንቦችን ይዟል። የአዋጁ አንቀጽ 71 “ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ያለው ሚዲያ የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም የግል እጩዎች በምርጫ ወቅት ፍትሃዊ ሽፋን እንዲያገኙ አግባብነት ባለው ህግ መሰረት የተመዘገቡ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት” ይላል። በተመሳሳይ መልኩ የኢትዮጵያ ምርጫ አዋጅ ቁጥር 1162/2011 እጩዎች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች የመገናኛ ብዙሃንን ስለመጠቀም በተመለከተ ስላላቸው መብት ድንጋጌዎችን ይዟል።

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የግሉ ሚዲያ፣ የመንግስት መገናኛ ብዙሃን እና ምርጫን የሚዘግቡ ጋዜጠኞች የስነምግባር ደንብ የማውጣት እና የመቆጣጠር ስልጣን ተሰጥቶታል። በዚህም መሰረት ቦርዱ መመሪያ ቁጥር 02/2020 አውጥቷል። የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማ የምርጫውን ሂደት ስኬታማ ለማድረግ የጋዜጠኞችን መብት፣ የሞራል ግዴታዎች እና ሃላፊነታቸውን መቆጣጠር ነው። መመሪያው ምርጫዎች ፍትሃዊ፣ ሚዛናዊ እና ተአማኒነት እንዲኖራቸው ሚዲያዎች የሚጫወቱትንን ወሳኝ ሚና ከግምት ውስጥ ያስገባ ነው። ለዚህም መመሪያው ከምርጫ ጋር የተያያዙ

1 WHAT IS MEDIA ACCESS? Media Access Australia
2 Press and Election in Ethiopia. Yosef Girmay. 2005.

ይዘቶችን ለመዘገብ ለሚፈልጉ ሚዲያዎች ፈቃድ ማግኘትን የመሳሰሉ የአሰራር መስፈርቶችን እንዲሁም ሚዲያዎችን ሊኖራቸው የሚገባውን የስነ-ምግባር መስፈርቶችን አስቀምጧል። በተጨማሪም የመገናኛ ብዙሃን የምርጫውን ሁሉንም ሂደቶችን በተመለከተ መረጃዎችን የማግኘት መብት ተሰጥቷቸዋል። የመገናኛ ብዙሃኑ ዘገባቸውን በሚሰሩበት ወቅት ለሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች እኩል እድል የመስጠት እና የትኛውንም የፖለቲካ ፓርቲ፣ እጩ፣ የፖለቲካ እምነት ወይም አስተያየት ከመደገፍ ወይም ከመቃወም የመቆጠብ ኃላፊነት አለባቸው።

# የኅብረት ለምርጫ የሚዲያ ክትትል ክፍል


የኅብረት ለምርጫ የሚዲያ ክትትል ክፍል በ6ኛው የኢትዮጵያ አጠቃላይ ምርጫ ሂደት ውስጥ በሚዲያ የተላለፉ ክስተቶች ላይ የተመሰረተ፣ ተዓማኒ እና ተጨባጭ በሆኑ እውነታዎች ላይ የተመሰረተ የሚዲያ ክትትል ሪፖርት ለማዘጋጀት ጥረት አድርጓል። ከመጋቢት 2013 እስከ ጥቅምት 2014 ዓም፤ ህብረቱ ዘጠኝ አባላት ያሉት የሚዲያ ክትትል ክፍል በማቋቋም በዘጠኝ የብሮድካስት ሚዲያዎች ላይ የክትትል ስራ አከናውኗል። ዘጠኙ ሚዲያዎች ለክትትል የተመረጡት ባላቸው የመልከ ምድር ተደራሽነት ፣ የተከታይ ብዛት እና በሚዲያ ባለቤትነት (የመንግስት እና የግል) መሠረት ነበር። ኅብረት ለምርጫ ሚዲያዎች በምርጫ ሂደት የሰጡትን የአየር ሰዓት ሽፋን መጠን ለመረዳት የቁጥር (Quantitative) እና የአይነት (Qualitative) መረጃ ትንታኔ መንገዶችን ተጠቅሟል።

1. የኅብረት ለምርጫ የሚዲያ ክትትል ክፍል የቁጥር ትንታኔን በመጠቀምበመገናኛ ብዙሃን ለተመረጡ ርዕሰ ጉዳዮች የተሰጠውን አጠቃላይ የጊዜ መጠን ገምግሟል። ግምገማው በሚካሄድበት ወቅት ትኩረቱን ያደረገው ሲሰሩ የነበሩት ዘገባዎች ይዘት አዎንታዊ፣ አሉታዊ ወይም ገለልተኛ መሆናቸውን መለየት ላይ ነበር። ይህ ትንታኔ በምርጫው ሂደት ውስጥ የሚዲያው ዘርፍ ለምርጫ የሰጠው ሽፋን ምን ያህል እንደነበር ማሳየት አስችሏል።
2. ክፍሉ በቁጥር ዘዴዎች ሙሉ በሙሉ ሊታዩ የማይችሉትን ከሚዲያ ሽፋን ጋር የተገናኙ ጉዳዮችን ለመገምገም የአይነት ትንታኔን ተጠቅሟል። ይህ ትንታኔ እንደ የጋዜጠኝነት ዘይቤ፣ ምርጫዎችን ለመሸፈን ጥቅም ላይ የሚውሉትን የሽፋን ፎርማቶችን፣ የሴቶች ውክልና፣ የመራጮች ትምህርት እና የምርጫ አስተዳደር ሽፋንን ለመገምገም ያለመ ነው። ይህም በምርጫ ወቅት ስለነበረው የሚድያ ሽፋን ጥራት እና ገለልተኛነት በደንብ የተደራጀ አረዳድ እንዲኖር አድርጓል።

# በ6ኛው ጠቅላላ ምርጫ ወቅት የነበረ የሚዲያ ተደራሽነት ለምርጫ ባለድርሻ አካላት


## ለመራጮች ትምህርት የተሰጠ የሚዲያ ሽፋን

የመራጮች ትምህርት አነስተኛ የሚዲያ ትኩረት ከተሰጣቸው ርዕሰ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ነበር። ግኝቶቹ እንደሚያሳዩት የመራጮች ትምህርት ይዘት ያላቸው ጥቂት ማስታወቂያዎች ብቻ በፕሪሚየር-ጊዜ ክፍተቶች ይለቀቁ ነበር፣ እነዚህም ዜናዎች እንዲመርጡ ማበረታታትን ያለሙ ነበሩ።




# የፖለቲካ ፓርቲዎች በክርክር ውስጥ

የቴሌቭዥን ጣቢያዎች ባዘጋጁት የክርክር መድረክ ላይ 12 የፖለቲካ ፓርቲዎች የተሳተፉ ሲሆን ይሁን እንጂ በክርክሩ የአንበሳውን ድርሻ ይዞ የነበረው ከ12 ክርክሮች በ8ቱ ላይ የተሳተፈው ገዢው የብልፅግና ፓርቲ ነበር። ይህም በምርጫው ሂደት ወቅት ለተለያዩ የምርጫ ባለድርሻ አካላት ያለተመጣጠን ሽፋን እንደተሰጠ አንድ ማሳያ ነው።





# የሽፋን ዘገባዎች

በጥቅሉ በሚዲያ ለፖለቲከኞች የተሰጠው ሽፋን መድሏዊ ያልነበረ እና የፖለቲካ ቡድኖችን በአዎንታዊ መልኩ ሽፋን የሰጠ ነበር። ሆኖም በተወሰነ መልኩ ሚዲያዎች በተለይም በአዲስ አበባ መገናኛ ብዙሃን፣ በአማራ ቲቪ እና ዋልታ ቲቪ የተላለፉ ዘገባዎች ለፖለቲካ ግለሰቦች ወይም ቡድኖችች ገለልተኛ ያልሆነ አለፍ ሲልም አሉታዊ ሽፋኖችን ሰጥተዋቸዋል። ከዚህም በተጨማሪ እነዚህ ሚዲያዎች አብዛኛውን የአየር ሰአታቸውን ለገዢው ፓርቲ ከፍተኛ የሆነ አዎንታዊ ዘገባ በመስራት ላይ አውለዋል። ይህ በስድስተኛው ጠቅላላ ምርጫ የነበረን ግልጽ የሆነ የፖለቲካ እና የምርጫ ወቅት ዘገባ እንደነበር ያሳያል።



# ለሴቶች የተሰጠ የሚዲያ ሽፋን

በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ከሴቶች ጋር ለተያያዙ ጉዳዮች ተስጥቶ የነበረው ሚዲያ ሽፋን በጣም አናሳ ነበር። በአሃዝ ለማሳየት ያህል በ27 ዙር በተደረጉ የምርጫ ክርክሮች ላይ 130 ተከርካሪዎች የቀረቡ ሲሆን ከእነዚህ ተከራካሪዎች ውስጥ የሴቶች ቁጥር ከ20 በመቶ ያነሰውን ብቻ ይወክላል። እነዚህ ሴት ተከራካሪዎችም የተወከሉት ከብልጽግና ፣ የኢትዮጵያ ዜጎች ማህበራዊ ፍትህ ፓርቲ እና ከነፃነት እና እኩልነት ፓርቲዎች ነበር።




# መደምደሚያ

በኢትዮጵያ የምርጫ እና የሚዲያ ህጎች መሠረት መገናኛ ብዙኃን ስለ ምርጫ እና በምርጫ ሂደት ስለሚሳተፉ አካላትአካላት ፍትሃዊ እና ገለልተኛ ሽፋን የመስጠት ግዴታ ተጥሎባቸዋል። በ6ኛው የኢትዮጵያ ጠቅላላ ምርጫ የሚዲያው ዘርፍ ዘገባዎች አንዳንድ አዎንታዊ ገጽታዎች የነበሩትን ያህል አንዳንድ ሊስተካከሉ የሚገባቸው አሳሳቢ ሁኔታዎችም ነበሩ። ከዚህ ጋር ተያይዞ ሊነሳ የሚችለው አቢይ ጉዳይ ለመራጮች ትምህርት የተሰጠው አነስተኛ ትኩረት ነው። ሌላው እዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ገዢው የብልጽግና ፓርቲ በክርክሮቹ ጊዜ የተሰጠውና ፍትሃዊ ያልሆነ ከሌሎች ፓርቲዎች የበለጠ ጊዜ ነው። አካታችነት በተመለከተ ሚዲያው ለሴቶች በቂ ሽፋን አለመስጠቱ ሴቶች በፖለቲካው ሂደት ውስጥ ዝቅተኛ ውክልና እንዲኖራቸው አስተዋጽኦ ሊያደርግ ስለሚችል በጣም አሳሳቢ ነው።

# ምክረ ሃሳቦች

## ምክረሃሳቦች ለሚዲያዎች እና ጋዜጠኞች

1. ህብረተሰቡን በድምጽ አሰጣጡ አስፈላጊነት እና እንዴት መምረጥ እንዳለበት ለሚያስተምሩ ፕሮግራሞች ተጨማሪ የአየር ጊዜ እና ግብአቶችቶች ማቅረብ ለመራጮች ትምህርት ቅድሚያ በመስጠት።
2. ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ክርክሮች ላይ ፍትሃዊ የአየር ሰአት ክፍፍል እና የመሳተፍ እድል ሊሰጣቸው ይገባል።
3. ፖለቲካ እና ምርጫ ላይ የተመሠረተ ዘገባን ለማቅረብ ሚዛናዊ እና ኢ-አድሎአዊ አካሄድን መከተል ፣ የትኛውንም የግል አስተያየት ወይም እምነት ከመሰንዘር መታቀብ።

## ለመንግስት እና ለመገናኛ ብዙሃን ባለስልጣናት የተሰጡ ምክረሃሳቦች፡-

1. የሚዲያ ተቋማት በምርጫ ወቅትወቅት ፍትሃዊ እና ገለልተኛ ሽፋን እንዲሰጡ እና የሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች እኩል ውክልና እንዲኖራቸው የሚጠይቁ ደንቦችን ማስከበር።
2. የመገናኛ ብዙሃንን ብዝሃነትን እና አካታችነትን እንዲያበረታቱ መድገፍመድገፍ

## ምክረሃሳቦችሳቦች ለሲቪል ማህበራት ድርጅቶች እና የጋዜጠኞች ማህበራት ምክሮች፡-

1. ብዝሃነትን እና አካታችነትን የሚያራምዱ ህጎች እና ፖሊሲዎች እንዲወጡ እንዲሁም ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ክርክሮች ላይ ፍትሃዊ ውክልና እንዲኖራቸው መሟገት።
2. ብዝሃነትን እና አካታችነትን የሚያራምዱ ህጎች እና ፖሊሲዎች እንዲወጡ እንዲሁም ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ክርክሮች ላይ ፍትሃዊ ውክልና እንዲኖራቸው መሟገት።

## ለፖለቲካ ፓርቲዎች ምክሮች፡-

1. በምርጫ ክርክሮች ውስጥ ፍትሃዊ እና እኩል ውክልና እንዲኖር መጠየቅ እና ለተገለሉ ቡድኖችን ውክልና ቅድሚያ መስጠት።
2. በፓርቲያቸው ውስጥ ብዝሃነት እና አካታችነትን ማሳደግ እና ሴቶችን ለአመራር ቦታዎች መመልመል እና እንዲበቁ ማድረግ።

በ6ተኛው ጠቅላላ ምርጫ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ ተቋም(NDI) የኅብረት ለምርጫን  የዜጎች ምርጫ ትዝብት ተግባራትን የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ ይህ የፖሊሲ ምክረ - ሃሳብ ታትሞ ሊወጣ የቻለው እና የታተመው በአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ኤጀንሲ (USAID) በኩል ከአሜሪካ ሕዝብ በተበረከተ ቸር እገዛ ሲሆን ይዘቱ የኢትዮጵያ ሲቪል ማኅበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ(ኅብረት ለምርጫ) ኃላፊነት እንጂ የUSAID፣ የአሜሪካ መንግስት አመለካከት የሚያንፀባርቁ አይደሉም።

የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ(ኅብረት ለምርጫ) በኢትዮጵያ ለሚደረጉ ምርጫዎች የፖሊሲ፣ የህግ እና የተቋማዊ ማሻሻያዎች ምቹ ሁኔታን ለመደገፍ ይህንን የፖሊሲ ፍሬ ሃሳብ አዘጋጅቷል። ኅብረት ለምርጫ፤ በምርጫ ሂደት የህግ ማዕቀፎች እና የፖሊሲ ማሻሻያዎችን ለማበረታታት በእነዚህ ህትመት ውስጥ በማስረጃ ላይ የተመሰረተ፣ በፖሊሲ ላይ ያተኮረ ትንተና እንዲሁም ምክረ -ሃሳቦችን ተጠቅሟል፡፡


## የኢትዮጵያ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ኅብረት ለምርጫ

**ስድስት ኪሎ፣ ኢንተርናሽናል ሊደርሺፕ ኢኒስቲቲዩት ሕንጻ 2ኛ ወለል**
**አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ**

+251 11 811 1455
www.cecoe.org
info@cecoe.org
twitter: @cecoeEth
facebook: CECOE21